## *የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ !!*

ወያኔ ኢትዮጵያን ለ 27 ዓመት የገዛው በጀግንነቱ ወይም በእውቀቱ እንዳልሆነ ምስክሮች እኛው ራሳችን ነን፣ እኛ ለዚህ ውርደት የበቃነው ወያኔ ከሕዝባችን ከሚዘርፈው ጥቂቱም ለአንዳንድ ሆዳሞች በማጉረስ እንደሆነ ለማንም እትዮጵያዊ ግልጽ ነው፡፡ መዝረፉ አለመጠ እይሰፋ፣ ንብረት ወደ ትግራይ ማጋዙ ተጠናክሮ በመቀጠሉ፣ ገዳይና አስገዳይ እየበዙ፣ ስደትና አገር ጥሎ መሸሽ፣ ወዘተ ዕድሉ የሆነ ሕዝብ ፡፡ጅብ ከሚበላህ ጅብ በልተህ፡፡ ተቀደስ እንደተባለ ሁሉ ፀረ ወያኔ ትግል ከየአቅጣጫው ሲጀምር ተዳፍኖ የኖረ የማንነት ጥያቄ የጎላ ሥፍራ መያዝ ጀመረ፡፡ የወልቃይት የማንነት ጥያቄ በመላ አገራችን መቀጣጠል ሲጀምር የኦሮሞ ወጣቶችና የአማራ ወጣቶች ግንኙነት ከንድፈ ሐሳብ ወደ ተግባርሲቀየር ወያኔ ክፉኛ ተርበደበደ፣«እሳትና ጭድ እንዴት ተስማሙ» ብለው ቢቆዝሙም የለውጡ ቋያ እንዳይበሏቸው መቀሌ ላይ ከሁለት ወር በላይ ኮምሲዮን ተቀምጠው ሥልጣን ለታማኛቸው ሰጥተው ንብረታቸውን ወደ መቀሌ ማሸሽ ጀመሩ፡፡ጉዳዩ በዕርግጥ ቀደም ተብሎ መተካካት በሚል ስልታዊ በዘር የሥልጣን ሽግግር ለማድረግ የታሰበ መሆኑ ለማንም አያጠራጥርም፡፡ የዶር አቢይ ወደ ሥልጣን መደየም ከዚሁ ደካማ ፍልስፍና ዉጤት የመጣ መሆኑን ብዙ ይፖለቲካ ሰዎች ያነሳሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስተራችን ወያኔዎች ሥልጣን በቸሩት ማግስት የወያኔ ፓርላማ ተብየውን ሣያማክር አጎራባች ክልሎችን ሰላም ሣይላቸው ረግጧቸው  ትግራይ ሄዶ ታማኝነቱን ገልጾ ተመልሶ ሌሎችንም ጎበኛቸው፣ ሲቃ ይዞት የነበረው የወያኔ የሥራ አመራር ከፍርሃት ነፃ ሆኖ በሰከነ አካሄድ ወደ ትግራይ አዘገመ፥ በከፍተኛ ወንጀል የሚፈልጉ የወያኔ በዶር አቢይ ተዕዛዝ የጡረታ መብታቸው ተከብሮ ግማሾቹ መቀሌ የቀሩት አሜሪካና ኤውሮፓ በዘረፉት ገንዘባችን የተቀማጠለ ኑሯችውን እየመሩ ከዚያም አልፈው ኢትዮጵያን የሚያውኩ ኃይል አሠማርተው እነሆ እንድንጠፋፋ እያጋደሉን ናቸው፡፡ በተጨማሪም ዛሬ መቀሌ ሆነው በኢትዮጵያ .ላይ ጦርነት እያወጁም ናቸው፣ ይባስም ብለው ከኢሕአዴግ ስብሰባም እየቀሩ ናቸው፣ ለምን ቀራችሁ ለምን ቀራችሁ ብሎ የምጠይቅ አካል ባለመኖሩ እንዳሻቸው እያደረጉ ናቸው፡፡

ዶር አቢይም ምንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ውክልና ባይኖረውም በቦታው እስከተቀመጠ አገራችን ከእርሱ የምትፈልገውን ከማከናወን ይልቅ ከኦሮሚያ አመራር ጋር በመሆን የኦርሚያን ክልል ነፃ ለማውጣትና ፊንፊኔ የኦሮሞ ጥቅም ማጠበቂያ መሆን አለበት በማለት እየማሰነ ይገኛል፥ ዶር አቢይ ባለፈው ሣምንት የእርሱ ደጋፊ የሆኑትን(እነ  ዳዉድ፣ እነ ፕ ር መረራን ሣይጨምር )ሌሎች ኦሮሞዎችን

በመሰብሰብ «የትግላችን መነሻ ፊንፊኔን ለኦርሞ ጥቅም ማስጠበቂያ ማድረግ፣ከዚያም ሌሎችንም ደረጃ በደረጃ ወደ ኦሮሚያ መመለስ ነው» በማለት የተናገርውን« ዘዳግም ኢትዮጵያ ፌስቡክ ላይ» ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ነገሩ አስቂኝም ነው፣ ለዚህ አንድ የኦሮሞ የፖለቲካ ምሁር የተናገሩትን *ብንጠቅስ«ናዝሬትን አዳማ፣ ደብረ ዘይትን ብሾፍቱ ብሎ መጥራት ይቻላል፥አዲስ አባባን ፊንፊኔ ብሎ ጠርቶ ለኦሮሞ የጥቅም ማስከበሪያ እናውላለን ብሎ መነሳት ዋጋ ያስከፍላል»*

ዶር አቢይ ወደ ሥልጣን እርካብ ከወጣ ጀምሮ የሠራቸው በጎ ሥራዎችን እንዲሁም ሆን ብሎ በቸልተኝነት በአገር ላይ ጉዳት ደርሷል፣ ይፋ የሆኑትን በቀመር ቢሞከር በእርግጥ ዶር አቢይ ሐቁ ይህ ነው ተብሎ ሲነገረው <<ማጣላት ቀላል ነው ማስታረቅ ግን ከባድ ነው«>> ብሎ ከሩቅ ስለሚዋጋ ገንቢ ሐሳቦችን ለመስጠት ይቸግራል፡፡ አዎን ስለአገራችን ያገባናል ብለን ስለምናምን ሐሳብ ከመስጠት ወደ ኋላ አንልም፡፡

1 ዶር አቢይ ብዙ እሥረኞችን ፈቷል፣ ከ3000 ያላነሱ የአዲስ አባባ ወጣቶችን ግን ያለምንም ጥፋት አሳስሯቸዋል፡፡

2 ዲያስፖራ ወደ አገር እንዲገቡ አድርጓል፣ ኢትዮጵያ የማታገኘውን ኢንጂኔር ስመኘው በቀለን ግን በጠራራ ፀሐይ በጥይት ተገድሏል፣ ገዳዮቹ እንኳንስ ለፍርድ መቅረብ ቀርቶ ቃላቸውን አልሰጡም፡ ፡

3 ከጂጂጋ ለተፈናቀሉ ኦሮሞች ከአዲስ አባባ ቤት አሰጥተዋቸው ሲያቋቋም በጂጂጋ ስለወደሙ አብያተ ክርስቲያናት፥ ስለተገደሉ ቀሳውስት እና ስለኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት መጨፍጨፍ ሰምቶ እንዳልሰማ፣ አይቶ እንዳላየ አልፎታል፡፡

4 ዶር አቢይ በቃል የሕዝቦችንን መፈናቀል ሲያወግዝ ከቡራዩ ስለተፈናቀሉት ጉዳዩ ይጣራል ከማለት ሌላ እርምጃ ለመውሰድ የቃጣው አንዳችም ነገር የለም፡፡

5 ዶር አቢይ በኤርትራ ጉዳይ የወሰደው አቋም በጎ ቢሆንም፥ ስለስምምነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተገለፀ ነገር አለመኖሩ ብዙዎች በቅሬታ ያነሱታል፡፡ ለእርቁም ከፕሬዝዳንት ኢሰያስ ጋር ወደ ሳውዲት አረቢያ ሄደው ተፈራርመው ተመለሱ እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተገለጸ ጉዳይ የለም፣ በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለባድሜ ጦርነት በውል ባያውቅም <ተነስ አገርህ ተወርራለች>> ሲባል <<ለምን?>> የሚለውን ጥያቄ ለማቅረብ ጊዜም አላገኘም፣ መብትም አልነበረውም፣ በመሠረቱ ዶር አብይ የወያኔ አመራር ስለነበረ እንለፈው ቢባልም ያን ጊዜ የተጀመረ ጉምጉምታ ውስጥ ውስጡን ሲንቀሳቀስ ኖሯል ፡፡የባድሜ ጦርነት ብዙ ሕይወት ቢቀጥፍም ለዛሬ ደርሶ ፍሬው ከኢሕአዴግ መንጋጋ ወጥቶ ከዶር አቢይ በመውደቁ ከመጎልበት ኢሕአአዴግ በአዲስ መልክ እየተጠናከረ የወያኔ ሕገ መንግሥትም እንደማይነካ ዶር አቢይ ለኢትዮያ ሕዝብ ገልፆታል......ትግሉ ወዴት ያመራ ይሆን ?????

6 ዶር አቢይ ዲያስፖራው ለኢትዮጵያ ልማት ገንዘብ እንዲያዋጣ ጥሪ አቅርቦ ከፊሉ ስኬታማ ሆኗል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ታሪክ ቀርቶ በዓለም ላይ ታይቶ የማይታወቅ የባንክ ዘረፋ በም ዕራብ ኢትዮጵያ ተካሂዶ ከ18 ባንኮች በላይ ሲዘረፉ ብዙ የመንግሥት ሠራተኞች መታገታቸው ከቦታው እየተሰማ ነው፣ስለደረሰ ጉዳትም ሆነ በደል የዶር አቢይ መንግሥት ተከታትሎ ወንጀለኞችን መያዝ አልቻለም፣ሕዝቡንም ከመሞት መታደግ አልቻለም፡፡

7 ዶር አቢይ መገዳደልን በማውገዙ ይደነቃል፣ የደቡብ ሕዝቦች ሲጨፋጨፉ፣ጎንደር ሲቃጠል ቃል ትንፍሽ አላለም፣ይህ ሕዝብን ብቃት ካሆን ፍላጎት እንደሌለው ያሳያል፡፡

8 ዶር አቢይ በጎ ሥራዎችን ቢያቅድም የኢትዮጵያን ሕዝብ ማማከር ዝቅተኝነት ይመስለዋል፣ ለምሣለ ጣልያን አገር ሄዶ የጣልያን መንግሥት ከምፅዋዕ እስከ አ አ የባቡር መንገድ እንዲሠራ ተስማምቶ መምጣቱ ተሰማ፣ ምፅዋዕ የኤርትራ ግዛት ናት፣ እንዴት ይሆናል? እዳውንስ ማን ይከፍላል? ልብ ይበል የኢትዮጵ ሕዝብ!!

9 ተደመሩ በሚለው የሚለውን ጥሪ ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ የሄዱት ያለ ምንም ክፍያ አገሪቱን ለመርዳት ሥራ የጀመሩ በአግባቡ መሥራት ባለመቻላቸው ሥራውን ጥለው የተመለሱ በርካታ ናቸው፡፡ በምትኩ ከውጭ ተደመርን ለሚሉት ለብዙዎች በየቀኑ 500 ዶላር እየተከላቸው ነው፡፡

10 በአጠቃላይ ዶር አቢይም ሆነ ብሎ የአንድ ፓርቲ ካቢኔው ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ብቃት እንዳለው ሲታወቅ ኢትዮጵያን ለመምራት ፍላጎት እንደሌለው ተገንዝቦ በደሙ የመጣውን ለውጥ የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ዛሬ ወቅቱ የሚጠይቀው የክልል ወይም የድንበር ጥ ያ ቄ የመኖር ወይም ያለመኖር ነው፡፡ይህን መጣጥፍ ለአንባቢያን ያቀረብነው ዶር አቢይን ወይም ካብኔውን በጥላቻ መልክ ሣይሆን በክንውን ላይ የሚገኘው እንቅስቃሴ አስጊ መስሎ ስለታየን ነው፡፡ ስለሆነም በደም የተገኘ ለውጥ ተጥናክሮ እንዲቀጥል የመላ ኢትዮጵያዊ ግዴታና ኃላፊነት መሆኑን አበክረን እንሳስባለን!!

## ኢትዮጵያ አንድነቷ ተጠብቆ ለዘላዓለም ትኑር !!

## አንድነታችን ይጠንክር !!